# ‵ወጣቱ የደርግ አባል’ መቶ አለቃ እሸቱ አለሙ በሆላንድ ታሰረ – የአለማቀፍ ወንጀል ችሎት ጉዳዩን ይዞታል

18 October 2015



በደርግ ዘመን በተለይ በጎጃም ክፍለ ሃገር ዜጎችን በመግደል፣ በማሰርና በማሰቃየት ተከስሶ የሞት ፍርድ የተበየነበት መቶ አለቃ እሸቱ አለሙ፤ ከትላንት በስትያ በሆላንድ- አምስተልቬን ከተማ በፖሊስ ቁጥጥር ስር መዋሉን ከሆላንድ ፖሊስ ለመረጋገጥ ችለናል፡፡

ክሱ የተጀመረው ከዛሬ **15** አመት በፊት ሲሆን በወቅቱ ከገዥው ፓርቲ ደህንነት ሃላፊ የነበሩት አቶ ክንፈ በተወካዮቻቸው አማካይነት ግፊት ማድረግ ጀምረው ነበር፡፡ ግፊቱ በሆላንድ የኢትዮጵያውያን ማህበር በኩል እንዲሆንም ጥያቄ ቀርቦ ነበር፡፡

በወቅቱ የነበረው የማህበሩ አመራር “ግለሰቡ መዳኘት ካለባቸው ዘ ሄግ ያለው አለም አቀፉ ፍርድ ቤት ነው” ሲል ጥያቄውን ውድቅ በማድረጉ ጉዳዩ ተቋርጦ ሰነበተ፡፡

ከጥቂት አመታት በኋላ ጉዳዩን የሆላን ጋዜጠኞች ይዘውት አምስተርዳም ያሉ ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች ጋር ሲመክሩ እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡ ከዚያም ጉዳዩ በሆላንድ የሚገኘው የአለማቀፍ ወንጀሎች ምርመራ ቡድን አቃቤ ህግ ጋ ደረሰ፡፡ የአለማቀፍ ወንጀሎች ምርመራ የአይን ምስክሮችን ከጎጃም እንዲሁም በውጭ አገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በመስማት ግለሰቡ እ.ኤ.አ በ **1978** ባስተላለፉት ትዕዛዝ፣ በደብረ ማርቆስና በመተከል ታስረው የነበሩ በርካታ ሰዎች ተረሽነው አስከሬናቸው በጅምላ እንዲቀበሩ አድርጓል የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ተጠርጣሪውን ከሁለት ሳምንታት በፊት በፖሊስ ቁጥጥር ስር አውሎታል ፡፡

አምስተልቬን ከተማ ውስጥ በሚገኘው የግለሰቡ መኖሪያ ቤት ውስጥ በተደረገ ፍተሻ የተለያዩ ማስረጃዎች የተገኙ ሲሆን የደርግ አባልነት ማረጋገጫ መታወቂያ እና የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት በኤግዚቢትነት ተይዘዋል። በሄግ የሚገኘው አለምአቀፎ ፍርድ ቤትም ከትናንት በስቲያ በዋለው ችሎት፣ ግለሰቡ ለ **90** ቀናት በእስር ላይ እንዲቆይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አቶ እሸቱ **61** አመታቸው እንደሆነ የያዙት ፓስፖርት ያሳያል። ዋሪነታቸውን በሆላንድ ሲሆን የአገሪቱ ዜግነትም አግኝተዋል። ግለሰቡ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት በሌሉበት የእድሜ ልክ እስራትና የሞት ቅጣቶች እንደተበየነባቸው የሚታወስ ነው፡፡

የሆላንድ መንግስት በጦር ፍርድ የተመሰከረባቸውን የተለያዩ ሃገራት ዜጎችን በማሰር ወደመጡበት ሃገር እየመለሰ ይገኛል፡፡ የሰው ደም ይጠራል የሚሉት አባባል እውነት ነው። የደርግ ባለስልጣናት ቅጣታቸውን ፈጽመው ከእስር ሲወጡ ነው እሸቱ የታሰረው። ይህ ይሆናል ብሎ ያሰበም አይመስልም። የሰውን ልጅ ደም በከንቱ ለሚያፈሱት ሁሉ ትልቅ ትምህርት ይሆናል።